# + አበገደ +

## ፊደልና ፊደላዋሪያ

## የልጆች አፍ መፍቻ።

## ከኪዳነ ወልድ ክፍሌ፤


በቅዱስ አልዓዛር ማተሚያ ቤት - ድሬ ዳዋ።

፲፱፻፴፬ ዓ.ም (1934)

ዳግመኛ ታተመ በአርቲስቲክ ማተሚያ ቤት

፲፱፻፵፰ ዓ.ም (1948) ፭ኛ መጣፍ።



NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# + አበገደ +

# ፊደልና ፊደላዋሪያ
# የልጆች አፍ መፍቻ።


## ከኪዳነ ወልድ ክፍሌ፤



በቅዱስ አልዓዛር ማተሚያ ቤት - ድሬ ዳዋ።

፲፱፻፳፮ ዓ.ም (1934)


ማርያም ድንግል ምስለ ፍቁር ወልዳ


ነቅዐ ጽጌ ረዳ



ወርግብ ጸዐዳ


መፍቅሪተ ፊደል አቡጊዳ።

ዳግመኛ ታተመ በአርቲስቲክ ማተሚያ ቤት



አለቃ ፡ ኪዳነወልድ ፡ ክፍሌ።

# ያርእስትና የክፍል የገጽ ቍጥር።


| **(አርእስት)** | **(ክፍል)** | **ገጽ** |
| --- | --- | --- |
| ፩ኛ ፊደል ከነመቅድሙና ከነጓዙ። | 1፫ | ፪-፲፯። |
| ፪ኛ ፊደላዋርያ ከነመቅድሙ። | ፪ | ፲፰-፳፰ |
| ፫ኛ የነቍጥና የነጥብ የንባብ ስሞች። | ፩ | ፳፱። |
| ፬ኛ ሶርያዊና ዕብራዊ ዐረቢ ፊደል። | ፩ | ፴። |
| ፭ኛ ማስረጃና ማስታወቂያ። | ፩ | ፴፩-፴፪ |

ፊት በታተመው ፊደል ባ፲፪ኛ ገጽ (ፊደል ስለ ታጣ በዝርዝር የተጣፉ አሉ፤ እሊሁም ጁዋ ዡዋ ኍዋ ኙዋ ናቸው)። ዳግመኛም በ፴፪ኛው ገጽ (የሱርስትም ፊደል መልኩ ይለይ እንጂ ስሙና ተራው እንዲሁ ነው፤ የፊደሉ ቅርጽ ስለ ታጣ ከወንድሞቹ ተለይቶ ቀርቷል) የሚለውን ቃል ያማርኛውንና የሱርስቱን ፊደል ቅርጽ በማግኘታችን ትተነዋል።

ይህን ፊደል ባ፲፱፻፳፰ ዓ.ም ፋሺስቶች በድሬ ዳዋ ስላቃጠሉት ከጥቂቶቹ ሰዎች በቀር ብዙዎቹ ሳያገኙት በመቅረታቸው እያዘነ የሱርስት ፊደል ጨምሮ በጥንቃቄ ዐርሞ ፩ኛ ያሳተመው

ደስታ ተክለ ወልድ ነው።

# መቅድም።

በስመ እግዚአብሔር ኀዳፍ ፈታሔ በሃም አፍ ወመርትዔ ልሳን ጻያፍ ንዌጥን በጽሒፍ ነገረ አሌፍ ጥንተ ፊደል ወጥንተ መጽሐፍ። አሜን።

ፊደልና ጥፈት በ፫ኛው ትውልድ በሄኖስ ዘመን ተዠምሯል። እግዜር ለሙሴ ዐሥርቱ ቃላትን በጽላት ጥፎ እንደ ሰጠው ለሄኖስም ፳፪ቱን አሌፋት በ፳፪ቱ፤ ሥነ ፍጥረት አምሳል በጸፍጻፈ ሰማይ ጥፎ አሳይቶ እንደ ፎቶግራፍ ወዲያው በልቡ ሥሎበታል። ከዚያ ወዲህ ጥፈትና ትምህርት የጥፈት ሥራ እየሰፋና እየበዛ ኼዷል። ይህም ታሪክ በኩፋሌና በሔኖክ ይገኛል። ኋላም ከአዳምና ከሄኖስ እስከ ራግው ድረስ ፩ የነበረው ፊደልና ቋንቋ ከባቢሎን ግንብ ተለያይቶ ቋንቋው እስከ ፸፪፤ ፊደሉ እስከ (፳) ኻያ ተከፍሏል። ከ፸፪ቱ ቋንቋ ፳፯ቱ የሴም፤ ፴፪ቱ የካም ፲፯ቱ የያፌት፤ ናቸው። ከኻያውም ፊደል ፰ቱ የሴም ፮ቱ የካም ፮ቱ የያፌት ይባላሉ። ትርጓሜ ፊደል የሚባለው አንቲካ መጣፍ ኹሉን በየስሙ ለይቶ ቈጥሮ ይናገራል። የኛም ፊደልና ቋንቋ ዘራችንና ትውልዳችን ሳይቀር ከየመን ከነገደ ዮቅጣን የመጣ (ዘፍ፲ ፳፯-፴፩) ፍጹም ሴማዊ ስለ ኾነ ከዕብራይስጥና ከሱርስት ከዐረብ ጋራ ይስማማል። እነዚህ ፬ቱ ቋንቆች እንዳራቱ ወንጌል በንባብ በምስጢር በፊደል ሳይቀር በኹሉ ፩ ናቸው። ከዚህ ይልቅ ደግሞ ግእዝ ማለት አንድ አንደኛ መዠመሪያ በኵር ቀዳማይ ገር ቅን ማለት ስለ ኾነ፤ የሴም ቋንቋ ጠልቀው ጠንቅቀው አካተው ፈጽመው ከማያውቁ ከጀርመን ሊቃውንት ስሙንና ግብሩን ተከትለው ግእዝ የአዳም ቋንቋ ነው የሚሉ አሉ። የግእዝና ያማርኛ ፊደል አንዳንዱ ኀርመት በነቍጣና በዋየል ፈንታ ቅጥላምና ቀለበታም ሰባራና ዐንካሳ በመኾን ራሱን ችሎ ድምጡና መልኩ ፯ ፯ ዐይነት ፯ ፯ ስልት ስለ ኾነ በዚህ ላይ ደግሞ መንታ መንታ ቅጥል ያላቸው ብዙ ዲቃሎች ስላሉት ኀርመቱን ወይም ቅንጣቱን በትኖ ዘርዝሮ ሲቈጥሩት ከአኃዙ በቀር ፪፻፸ ነውና በብዛቱና በትምህርቱ ልጅ እንያሰቅቅ ወዲያውም ቶሎ እንዲያውቅ ባ፲፫ ክፍል ተከፍሏል። አንዳንዲቱን ክፍል በንባብ በጥፈት ሳያጠኑና ሳያውቁ እጅ

ሳያደርጉ ወደ ሌላው ማለፍ በዚያው በዱሮው ሕግ ሳይቈርሱ እንደ መጕረሥ ነውና ተማሪ ይህነን ከማድረግ ይጠንቀቅ መምርም ይከልከል ይጠብቅ። ካ፲፫ኛው ክፍል በኋላ ፭ ክፍሎች አሉ። ፩ኛው፤ ግጥም የፊደላዋሪያ መቅድም። ፪ኛው፤ ሐዲስ ፊደላዋሪያ በግእዝና ባማርኛ። ፫ኛው፤ የነቍጣና የነጥብ የንባብ ስሞች። ፬ኛው፤ የሱርስትና የዕብራይስጥ የዐረብ ፊደል። ፭ኛው፤ ማስረጃና ማስታወቂያ ቃል። መላው የክፍሎች ቍጥር ፲፰ ነው።

# ፩ኛ ፊደል ከነመቅድሙና ከነጓዙ።

## የትምህርት ዐዋጅ በግጥም።

ስማ ስማ መምር ከነተማሪኽ፤
የተማሪ ቤትም ከነትምህርትኽ።
ግእዝ የማይሰማ ጥፈት የማያውቅ፤
ፊደል ከማስተማር ፈጽሞ ይራቅ፤
ላስተዋዩ ሕፃን ላይናማው ተማሪ፤
አያሻውምና ያይነ ስውር መሪ።
ልጆችም ይማሩ ካይናማ መምር፤
ጥፈትና ቋንቋ ከሚያስተባብር።
ዘር እንደ መኾኑ የፊደል ቅንጣት፤
ጥሩነት ያሻዋል በቃል በጥፈት።
አላዋቂ መምር ሲዘራው በቃል፤
ስንዴነቱ ቀርቶ ክርዳድ ይኾናል።
ተማሪ ሳይኾኑ መምር ነኝ ማለት፤
የፊደል ደመኛ የቋንቋ ጠላት፤
ከውነተኛው መንገድ ትምርትና ባህል፤

ሕፃናት ኹሉ የሚያስተዳጒል፤
መድኀኒት የሌለው ደዌና ድውይ፤
የልጆች ፈንጣጣ ወይም ሾተላይ።
ፈረሰኛው ትምህርት በኹለት ገመድ፤
እጁን እግሩን ታስሮ እንደ ምን ይኺድ፤
በኅይለ ሥላሴ በሉሉ በዘውዱ፤
ይፈታና ይጋልብ ይኺድ በመንገዱ፤
በሽምጥ አካኼድ ወይም በሱምሶማ፤
የተማሪው ኰቴ ከሩቅ እስኪሰማ።
ባላዋቂ ሐኪም እንዳይገኝ ፈውስ፤
ማንም ሰው ያውቀዋል ይህነን ስያስ።
ትምህርትና ጥፈት ሥምና ፈትል፤
ከተዋሐዱ ዘንድ አላቸው ጸዳል፤
የፊደልን ጠባይ የቋንቋን ምስጢር፤
በጣም የሚያስፈትሽ የሚያመረምር።
ያማርኛው ሰብል የግእዙ አዝመራ፤
ጭራሽ ተከቶልን በፊደል ጒተራ፤
ትምህርት እስኪያልፍልን ዕውቀት እስክንጠግብ፤
እጃችን ቃላችን አይላላ አይርገብ።
ፊደልን ከመጣፍ እጁ የሚዝል፤
ስንኳንስ መምርና ተማሪ አይባል፤

ስሙና ቀለቡ ላዋቂ ይሰጥ፤
ርሱም እንደ ገና ትምህርት ይቀላውጥ።

| የግእዝና ያማርኛ ፊደል። | | |
|---|---|---|
| (፩) ነጠላ ግእዝ። | | (፪) ድርብ ግእዝ። |
| **አ** | **መ** | **አበ** |
| **በ** | **ነ** | **ገደ** |
| **ገ** | **ሠ** | **ሀወ** |
| **ደ** | **ዐ** | **ዘሀ** |
| **ሀ** | **ፈ** | **ኀጠ** |
| **ወ** | **ጸ** | **የከ** |
| **ዘ** | **ዐ** | **ለመ** |
| **ሐ** | **ቀ** | **ነሠ** |
| **ኀ** | **ረ** | **ዐፈ** |
| **ጠ** | **ሰ** | **ጸፀ** |

| | | |
|---|---|---|
| የ | ተ | ቀረ |
| ከ | ጸ | ሰተ |
| ለ | ፐ | ጸፐ |

| (፫) ባለዲቃሎች። | (፬) ዲቃሎች ብቻ። |
|---|---|
| ገ-ጐ | ጐኍ |
| ኀ-ኈ | ኰቈ |
| ከ-ኰ | ጀዠ |
| ቀ-ቈ | ጨኸ |
| ደ-ጀ | ኘ(ኛ) |
| ዘ-ዠ | ሸቸ |
| ጠ-ጨ | |
| ከ-ኸ | |
| ነ-ኘ | |
| ሰ-ሸ | |
| ተ-ቸ | |

| ቁጥር። | |
|---|---|
| ፩ | ፮ |
| ፪ | ፯ |
| ፫ | ፰ |
| ፬ | ፱ |
| ፭ | ፲ |

## (፭)

| መላው ፳፮ቱ ፊደሎች ፯ ፯ቱ ከአ እስከ ፐ | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |

## (፮)

| የሰባቱ ፊደላት ስምና ቊጥር። | | | |
|---|---|---|---|
| አልፍ አ። | | | |
| አ- | ግእዝ | = አንደኛ- | ፩ኛ። |
| ኡ- | ካዕብ | = ኹለተኛ - | ፪ኛ። |
| ኢ- | ሣልስ | = ሦስተኛ - | ፫ኛ። |
| ኣ- | ራብዕ | = አራተኛ - | ፬ኛ። |
| ኤ- | ኃምስ | = አምስተኛ - | ፭ኛ። |
| እ- | ሳድስ | = ስድስተኛ- | ፮ኛ። |
| ኦ- | ሳብዕ | = ሰባተኛ - | ፯ኛ። |

ተመልሰኽ ከበ እስከ ፐ ያሉትን ፯ ፯ቱን ኹሉ እንደዚህ ቊጠር።

## (፱)

| ፬ቱ ዲቃሎች ፩ ፩ቱ። | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ገ) | ጐ | ጒ | ጓ | ጔ | ጒ |
| ኀ) | ኈ | ኊ | ኋ | ኌ | ኊ |
| ከ) | ኰ | ኲ | ኳ | ኴ | ኲ (ኸ፞) |
| ቀ) | ቈ | ቌ | ቋ | ቊ | ቌ |

## (፲)

| ቅንጁና ቀንጃ የንባብ መልመጃ። | |
|---|---|
| አኡ ኢኣ ኤእ ኦ። | ለሉ ሊላ ሌል ሎ። |
| በቡ ቢባ ቤብ ቦ። | መሙ ሚማ ሜም ሞ። |
| ገጉ ጊጋ ጌግ ጎ። | ነኑ ኒና ኔን ኖ። |
| ጎግ ጓጔ ግ - ። | ሠሡ ሢሣ ሤሥ ሦ። |
| ደዱ ዲዳ ዴድ ዶ። | ዐዑ ዒዓ ዔዕ ዖ። |
| ሀሁ ሂሃ ሄህ ሆ። | ፈፉ ፊፋ ፌፍ ፎ። |

| | |
|---|---|
| ወዉ ዊዋ ዌው ዎ። | ጸጹ ጺጻ ጼጽ ጾ። |
| ዘዙ ዚዛ ዜዝ ዞ። | ፀፁ ፂፃ ፄፅ ፆ። |
| ሐሑ ሒሓ ሔሕ ሖ። | ቀቁ ቂቃ ቄቅ ቆ። |
| ኀኁ ኂኃ ኄኅ ኆ። | ቈቍ ቊቋ ቌ - ። |
| ኈኍ ኊኋ ኌ - ። | ረሩ ሪራ ሬር ሮ። |
| ጠጡ ጢጣ ጤጥ ጦ። | ሰሱ ሲሳ ሴስ ሶ። |
| የዩ ዪያ ዬይ ዮ። | ተቱ ቲታ ቴት ቶ። |
| ከኩ ኪካ ኬክ ኮ። | ጰጱ ጲጳ ጴጵ ጶ። |
| ኰኵ ኲኳ ኴ - ። | ፐፑ ፒፓ ፔፕ ፖ። |

(፱)

| ፯ቱ ዐማርኞች ብቻ ፯ ፯ቱ። | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |

| ቅንጁና ቀንጃ። | | | |
|---|---|---|---|
| ጀጁ | ጂጃ | ጄጅ | ጆ። |
| ዠዡ | ዢዣ | ዤዥ | ዦ። |
| ጨጩ | ጪጫ | ጬጭ | ጮ። |
| ኸኹ | ኺኻ | ኼኽ | ኾ። |
| ኘኙ | ኚኛ | ኜኝ | ኞ። |
| ሸሹ | ሺሻ | ሸሽ | ሾ። |
| ቸቹ | ቺቻ | ቼች | ቾ። |

(፲)

በጓኋኳቋ አንጻር ከግእዙም ካማርኛውም የሚገኙ አንዳንድ ዲቃሎች ራብዖች ብቻ። ((እነዚሁም በሩቅ ሴት ዝርዝርና በስም በግብር በነገር ኹሎ ይገባሉ))።

| ከግእዙ። | |
|---|---|
| ባ - ቧ.............. ሥቧ | ሜ - ሟ............ንጉሟ |
| ዳ - ዷ............. ድዷ | ፋ - ፏ.............ግፏ |
| ዛ - ዟ............... ኋዟ | ፃ - ጻ - ጿ..........ጌጿ |
| ጣ - ጧ.............ቅጧ | ራ - ሯ........... ሥሯ |
| ላ - ሏ...............ቃሏ | ሳ - ሷ...............ርሷ |
| ማ - ሟ.............ደሟ | ታ - ቷ.............እቷ |
| ና - ኗ እሾኳ፡ | |

| ካማርኛው። | |
|---|---|
| ጃ-ጇ...............ግዳጇ | ኛ-ኟ..............ቀኟ |
| ዠ-ዧ...............ናዛዠ | ሻ-ሿ..........ወራሿ |
| ጫ-ጯ.............ግንጯ | ቻ-ቿ..........ላሞቿ |
| ኻ-ዃ...............እሾኳ | |

(፲፩)

| ፩ኛ የፊደል መንገድ በስያፍ አካኼድ፤ ዘረ ዝንቅ መልከ ድብልቅ። | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አ | ቡ | ጊ | ዳ | ሄ | ው | ዞ |
| በ | ጉ | ዲ | ሃ | ዌ | ዝ | ዦ |
| ገ | ዱ | ሂ | ዋ | ዜ | ሕ | ጦ |
| ደ | ሁ | ዊ | ዛ | ሔ | ፕ | ዮ |
| ሀ | ዉ | ዚ | ሓ | ጤ | ይ | ኮ |
| ወ | ዙ | ሒ | ጣ | ዬ | ክ | ሎ |
| ዘ | ሑ | ጢ | ያ | ኬ | ል | ሞ |
| ሐ | ጡ | ዪ | ካ | ሌ | ም | ኖ |
| ጠ | ዩ | ኪ | ላ | ሜ | ን | ሦ |
| የ | ኩ | ሊ | ማ | ኔ | ሥ | ዖ |
| ከ | ሉ | ሚ | ና | ሤ | ዕ | ፎ |
| ለ | ሙ | ኒ | ሣ | ዔ | ፍ | ጾ |
| መ | ኑ | ሢ | ዓ | ፌ | ጽ | ቆ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ነ | ሡ | ዒ | ፉ | ጼ | ቅ | ሮ |
| ሠ | ዑ | ፈ | ጻ | ቄ | ር | ሶ |
| ዐ | ፉ | ጺ | ቃ | ሬ | ስ | ቶ |
| ፊ | ጹ | ቂ | ሩ | ሴ | ት | ኖ |
| ጸ | ቁ | ሪ | ሳ | ቴ | ኀ | ዖ |
| ቀ | ኑ | ሲ | ታ | ኄ | ፀ | ጶ |
| ረ | ሱ | ቲ | ኃ | ዬ | ጵ | ፖ |
| ሰ | ቱ | ኂ | ፃ | ጴ | ፕ | ኦ |
| ተ | ኁ | ዪ | ጳ | ፔ | እ | ቦ |
| ኀ | ፁ | ጲ | ፓ | ኤ | ብ | ኅ |
| ፀ | ጱ | ፒ | አ | ቤ | ግ | ዶ |
| ጰ | ፑ | ኢ | ባ | ጌ | ድ | ሆ |
| ፐ | ኡ | ቢ | ጋ | ዴ | ህ | ዎ |

(፲፪)

| የሦስትና ያንድ ፊደል ንባብ እንደርሻ አካኼድ። | |
|---|---|
| አቡጊ ዳ ሄውዞ። | ነሡዒ ፋ ጼቅሮ። |
| በጉዲ ሃ ዌዝሖ። | ሠዑፊ ጻ ቄርሶ። |
| ገዱሂ ዋ ዜሕጦ። | ዐፉጺ ቃ ሬስቶ። |
| ደሁዊ ዛ ሔጥዮ። | ፈጹቂ ራ ሴትኖ። |
| ሀውዚ ሓ ጤይኮ። | ጸቁሪ ሳ ቴኖዖ። |
| ወዙሒ ጣ ዬክሎ። | ቀሩሲ ታ ኌዕጾ። |
| ዘሒጢ ያ ኬልሞ። | ረሱቲ ኃ ዜጽፖ። |
| ሐጡዩ ካ ሌምኖ። | ሰቱኊ ፃ ጼፕኦ። |
| ጠዩኪ ላ ሜንሦ። | ተኍፂ ጷ ፔእቦ። |
| የኩሊ ማ ኔሥዖ። | ኈፁጺ ፓ አብኅ። |
| ከሉሚ ና ሤዕፎ። | ፀጹፒ ኣ ቤግዶ። |
| ለሙኒ ሣ ዕፍጾ። | ጳፑኢ ባ ጌድሆ። |
| መኒሢ ዓ ፌጽቆ። | ፐኡቢ ጋ ዴህዎ፤ |

(፲፫)

| ቁጥርና የቁጥር ስም በፊደል ፤ በአኃዝ በግእዝና ባማርኛ። | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አ | አሐድ | ሐዱ። | ፩-1 | አንድ። |
| በ | ክልኤት | ቱ። | ፪-2 | ኹለት። |
| ገ | ሠለስት | ቱ። | ፫-3 | ሦ (ሠወ) ስት። |
| ደ | አርባዕት | ቱ። | ፬-4 | አራት። |
| ሀ | ኀምስት | ቱ። | ፭-5 | ዐምስት። |
| ወ | ስድስት | ቱ። | ፮-6 | ስድስት። |
| ዘ | ሰብዐት | ቱ። | ፯-7 | ሰባት። |
| ሐ | ሰመንት | ቱ። | ፰-8 | ስምንት። |
| ጠ | ሰስዐት | ቱ። | ፱-9 | ዘጠኝ። |
| የ | ዐሠርት | ቱ። | ፲-10 | ዐሥር። |
| ከ | ዕሥራ | (ሁ)። | ፳-20 | ካያ-ኻያ። |
| ለ | ሠላሳ | (ሁ)። | ፴-30 | ሠላሳ። |
| መ | አርብዓ | (ሁ)። | ፵-40 | አርባ። |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ነ | ኀምሳ | (ሁ)። | ፶-50 | ዐምሳ። |
| ሠ | ሰሳ | ስድሳ። | ፷-60 | ስሳ ሥልሳ። |
| ዐ | ሰብዓ | ---። | ፸-70 | ሰባ። |
| ፈ | ሰማንያ። | | ፹-80 | ሰማኒያ። |
| ጸ | ተስዓ (ሁ)። | | ፺-90 | ዘጠና። |
| ቀ | ምእት | (ቈ-አምኣት) | ፻-100 | መቶ። |
| ረ | ክልኤ | (ቱ) ምእት። | ፪፻-200 | ኹለት መቶ። |
| ሰ | ሠለስቱ | ምእት። | ፫፻-300 | ሦስት መቶ። |
| ተ | አርባዕቱ | ምእት። | ፬፻-400 | አራት መቶ። |
| ኀ | ኀምስቱ | ምእት። | ፭፻-500 | ዐምስት መቶ። |
| ዐ | ስድስቱ | ምእት። | ፮፻-600 | ስድስት መቶ። |
| ጰ | ሰብዐቱ | ምእት። | ፯፻-700 | ሰባት መቶ። |
| ፐ | ሰመንቱ | ምእት። | ፰፻-800 | ስምንት መቶ። |
| ኆ | ተስዐቱ | ምእት። | ፱፻-900 | ዘጠኝ መቶ። |


| | | | |
|---|---|---|---|
| ቈ | ዐሠርቱ | ምእት። | ፲፻-1.000 ዐሥር መቶ ሺ። |
| እ | እልፍ | -----። | ፼-10.000 ፻ጊዜ፻። ፲ሺሕ። |



# ፪ኛ ፊደላዋርያ ከነመቅድሙ።

## (፲፬)

ዘከመ መሀረ እግዚእነ ወልደ ዐሥርቱ ወክልኤቱ ዓመት ማእከለ ሊቃውንት ያነከሩ ምህሮቶ።



ጌታችን በሕፃንነቱ ለአይሁድ ሊቃውንት በጥያቄና በምላሽ እያስረዳ እንዳስተማራቸው ርሳቸውም እንዳደነቁት ( ሉቃ ፪ ፥ ፵፮ ፤ ፵፯)

# የፊደላዋሪያ መቅድም።

ተማሮች ከፊደል ጋራ በግጥም ቃል የተመላለሱት ፲፫ ክፍል። ጥያቄና ምላሽ ከነምልክቱ። ተ ተማሮች። ፊ ፊደል።

(፩)

(ተ) አንች አይደለሽሞይ ከግዜር ከባልሽ
ብሉይን ሐዲስን ቀድሞ የወለድሽ።
(ፊ) ታውቁታላችሆይ የልጆቼን ስም
የልጅ ልጆቼማ አይቈጠሩም።

(፪)

(ተ) እኛስ አናውቀውም ያንዱንም ያንዱን
እንዳወላድሽ አንችው ንገሪን።
(ፊ) ከኦሪት ዘፍጥረት ከግንባር ቀደሙ
እስካቡቀለምሲስ መቈረጫ ወንድሙ
በባለታሪኮች ሕግና ልማድ
ዛሬ ልንገራችኍ የለኝም ፈቃድ።
አኹንስ ለጊዜው ደስ እንዲላችኍ
ከፊደላዋሪያ ላስተዋውቃችኍ
በፊደላዋሪያም ጥቂት አቈይቼ

**አጋባችኋለኹ ከአዋልዶቼ።**

**(፫)**

**(ተ) ልጆች ለልጅ ልጆች የታጨንበት**
**በምን ምክንያት ነው በምን ምክንያት።**
**(ፊ) ይች የተጠቃችው ጊደሬ ግእዝ**
**ምናልባት መላልሳ ብትወልድ ብታረግዝ**
**አውራ ፊልጌ ነው ካዋልድ በኋላ**
**ብሉይና ሐዲስ ደፍሮ የሚበላ።**

**(፬)**

**(ተ) መጣፍ የሚበላ የመጣፍ ቀበኛ**
**ዛሬ በኛ ዘመን አይገኝም ከኛ**
**የመጣፉን ማኅበር ሽንጎና ጕባይ**
**የውጭ አገር ቋንቋ ወርሶት የለሞይ።**
**(ፊ) እኔ ተስፋ አልቆርጥም በጥቂ ግእዜ**
**ገና ብዙ ልትወልድ አላትና ጊዜ።**
**ምንም በቴዎድርስ ቢሞት ቢቀበር**
**መነሣቱ አይቀርም ትምርቷ አልዓዛር።**
**ኀይለ ሥላሴማ ግርማዊው አንበሳ**
**ግእዝ ያልተማረ እያለ ቢያገሣ**
**ስንኳን የናንተን ልብ ርጥቡን ሬሳ**
**ዱሮ የሞተውን ደረቁን ባስነሣ።**

**የውጭውስ ቋንቋ መች ይነቀፍና**
**የሚነቀፈውስ የናንተ ስንፍና።**
**ሰው በፊደሉ ላይ ቢጨምር ፊደል**
**ዐይናማ ይሆናል እንደ ኪሩቤል።**
**በቋንቋ ላይ ቋንቋ ብትጨምሩማ**
**ያድርባችኍ ነበር የሱራፌል ግርማ።**

**(፫)**

**(ተ) ሃይማኖት ያስለውጥ እየመሰለን**
**እጅግ አንወደውም ቋንቋ መማሩን**
**ከሃይማኖት ኹሉ የኛ ሃይማኖት**
**ትበልጣለችና በውነተኛነት።**
**(ፊ) የልጅ ነገር ወትሮ ፪ ቅንጣት ፍሬ**
**አንዱ ፍጹም ብስል አንዱ ፍጹም ጥሬ**
**አባቴ ታናሽ ነው ሃይማኖቴ ክፉ**
**የሚል የለምና በዚህ አትስነፉ።**
**ምንም ብዙ ቢኾን ስሙና ማኅበሩ**
**አንድ ክርስቶስ ነው የክርስቲያን በኵሩ።**
**በክርስቶስ ክርስቲያን የተባለ ኹሉ**
**የክርስቶስ መንጋ እንደ ኾነ አስተውሉ።**
**ኋላ በፍርድ ቀን እስኪለየው ፈርዶ**
**ኹሉ ዐብሮ ይግጣል የተስፋውን ሠርዶ።**

**የሃይማኖት ወንፊት የምግባር ስፌድ**
**በትእዛዙና በሕጉ መኼድ፤**
**ወንድምን እንደ ራስ አጥብቆ መውደድ፤**
**መች አንዱ ባንዱ ላይ መጓደድ መፍረድ።**
**የወንጌል ሃይማኖት ፍቅርና ትሕትና**
**ኹሉን ታስኬዳለች ባንድ አምላክ ጐዳና።**
**አንድ ወጣት ስልቻ በያገሩ ባህል**
**አቅማዳ ቀልቀሎ ለቄታ እንዲባል፤**
**የሃይማኖትም ስም ልዩ ልዩነቱ**
**ይህነን ይመስላል ቋንቋ ለሚያውቁቱ።**
**ቋንቋና እጅ ሥራ ካልጨመራችኹ**
**ንግድና መኪና ካላቆማችኹ፤**
**ባንድ ክፍል ትምርት በድኅ በቅኔ**
**አይገኙምና ብዕልና ሥልጣኔ፤**
**ይልቅስ ተማሩ ኹሉን በያይነቱ**
**ቶሎ እንዲለቃችኹ ስንፍናው ንዴቱ።**

**(፺)**

**(ተ) ቋንቋስ ይበቃናል ያባቶቻችን፤**
**ሥልጣኔው ብቻ ነው የሚያስፈልገን።**
**(ፊ) ትሰሙኝ እንደኾን ልንገራችኹ እኔ፤**
**አለቋንቋ ትምህርት ሥልጣኔ ስይጣኔ።**

የተዳፈነ እሳት የተፈጥሮ ዕውቀት
አይነድም አይነድም ካልገላለጡት
እንዲጤስ እንዲነድ እንዲበረክት
መጨመር ያሻዋል ኵበትና ዕንጨት፤
ኵበቱም ዕንጨቱም የጠበብ ትምርት
ኤውሮፖች በመጣፍ አለቃቀሙት።
እናንተም ለቃቅሙ ሰብስቡ በቅጥ
ቤታችኹ እንዲሞቅ እንዲገለምጥ፤
በቋንቋችኹ መጣፍ ባሮጌው ብራና
ሐዲሱ ሥልጣኔ አልተጣፈምና።

(፯)

(ተ) ኹለት ልዩ ቋንቋ ኹለት ምላስ
አያስነቅፍሞይ ባንድ ሰው ራስ።

(ፊ) ካላነሰ በቀር የውቀቱ ስልቻ
እንዳይና ማለት ነው አንድ ቋንቋ ብቻ።
ያንድ ዐይናማ ትርጓሜ እኩሌታ ዕውር፤
ያልተፈጸመለት የማየት ነገር።

በሥጋዊ ጥበብ የተመሠረተ
አንዳንድ ቋንቋ መማር ግድ ነው ለናንተ
ሦስት አራቱን ዳቦ ኹሉን ከመላስ
አንዱን መንከስ መግመጥ አጥብቆ መጐረሥ።

**(፳)**

**(ተ) ምንም ብንሞግትሽ ደፍረን ባለውቀት**
**ይገባናልና ያንችን ቃል መስማት፤**
**ባጭር ቃል አሳዩን ዐጭሩን መንገድ**
**ወደ ቋንቋው ትምርት ቶሎ እንድንኼድ።**
**(ፊ) ራስን ሳይዙ ወዳጅ አያበዙ፤**
**ይህነን ምሳሌ አጥብቃችኹ ያዙ።**
**ፊት ከውጭ ቋንቋ ከመተናነቁ**
**ግእዝ ቋንቋችኹን አስቀድሞ ዕወቁ።**
**ላቲን ለኤውሮፓ በግድ እንዲያሻው**
**ለኢትዮጵያም ግእዝ ግድ ነው።**

**(፳፩)**

**(ተ) የግእዝን ቋንቋ አጥርቶ መማር**
**ምን ክብር ያሰጠናል ከውርደት በቀር።**
**ሊቃውንትን ኹሉ ጨልጦ ገርኝቶ**
**ማነው ያሰደደ ካገር አሶጥቶ፤**
**እኛስ ብንማረው እንደነዚያ ኹሉ**
**ይሰድቡን የለሞይ መናፍቅ እያሉ።**
**(ፊ) የደብተራ ደዌ የዲያቆን የቄስ**
**የግእዝን ቋንቋ ጠንቅሎ መቅመስ፤**

**በመጽሐፍ ያለውን ጣዕምና ምረር**
**አያስለይምና ጠልቆ እንደ መማር፤**
**መናፍቅ ሳትኾኑ መናፍቅ ቢሏችኹ**
**ባላዋቆች ስድብ ምን ትጐዳላችኹ።**
**ሳያውቁ ከመክበር ዐውቆ መዋረድ**
**ስለ ሃይማኖትም በግፍ መሰደድ**
**የባለመክሊቶች የመምህራን ንግድ፤**
**በገበያው ዳኛ በክርስቶስ ዘንድ**
**ሲፈርስ ሲቈጠር ሲመዘን በፍርድ**
**ብዙ ትርፍ አለበት የወለድ ወለድ።**
**ዛሬ ግን አይዟችኹ ደፍራችኹ ተማሩ፤**
**የስድቡ ጊዜ ዐልፏል ከማእረሩ።**
**ጌታም ባርኳችኋል እንደነምናሴ**
**እጁን አስተላልፎ በኀይለ ሥላሴ፤**
**ኋላ ስታድጉለት በውድም በግድ**
**ሊቀ ጽጽስና ይሾማችኹ ዘንድ።**

(፲)

**(ተ) እየጐተተብን አንዱ ቃል አንዱን**
**ነገር በማሻሻል እዚህ ከደረስን**
**ርግፍ አርገን ትተን የያዝነውን ወሬ**
**መመለስ ይሻላል ወደ ቋንቋው ፍሬ።**

## (ፊ) ከየመን የመጣች የግእዝ ፊደል

የማን ትሰብካለች በየማናይ ቃል።
ካለም ቋንቋ ምስጢር እንድትሳተፉ
እነግራችኋለኹ ኹሉን በየረድፉ፤
የግእዙን መንገድ ከያዛችኹ ቀድሞ
ሌላው አይመክትም ከፊታችኹ ቁሞ።
የሴም ቋንቋ ሱርስት ዐረብ ዕብራይስጥ
ከዚህ አሉላችኹ በግእዙ ውስጥ።
የያፌትም ቋንቋ እንደ ወይን ዐረግ
ይሳብላችኋል በግእዙ ሕግ፤
በውስጡ ያለውን ዘለላ ትምርት
እንዳሥራ ኹለቱ ግቦኞች አርድእት
ባማርኛ ቀፎ በግእዝ ቅርጫት
ለቅማችኹ ቀሥማችኹ እስክታመጡት።
ቋንቋውን አጥቅቶ የተማረ ሰው
ችግር የለበትም በኹለተኛው።
አልሰማችኹሞይ ከቋንቋ ዐዋቆች
ባለም ቋንቋ ኹሉ በዘጠኝ ክፍሎች
ታውጇ ተነግራ ተጥፋ ያለች
የሰዋሰው መንገድ አንድ አንድ ኾነች።
አንድ ዐረግ ሲስቡ ዱር ይሰበስቡ

የተባለውን ቃል ስለ ቋንቋ ዐስቡ።

በዚህ ላይ መምሩ ያገር ልጅ ሲኾን

መሰወር አይችሉም ጥበብና ኪን

ያገር ልጅ የማር እጅ የሚሉት ተረት

ከመምር ከጳጳስ አለው መስማማት።

ንጉሥና ጳጳስ ግራና ቀኝ ዐይን

አንድ ዐይነት ሊኾኑ አይገባምን

ንጉሥ እያላችኹ ጳጳስ መበደር

ይኸ ነው የዘጋው የትምርቱን በር።

መበደሩ ቀርቶ ክህነትና አቡን

ሊቀ ጵጵስናው በጃችኹ ቢኾን፤

ኢትዮጵያችኹ እንደ ፀሓይ ሙቃ

ታንግብቡ ነበር አፍሪቃ ላፍሪቃ

ወደ እስያም ክፍል እንዳዬ ካሌብ

ትሻገሩ ነበር በወንጌል መርከብ።

ከሕዝብ ተመርጦ በትምርቱ ተስፋ

ልቅና የሚሾም ያገር ልጅ ሳይጠፋ፤

ክብርን አሳልፎ ለባዕድ መስጠት

ስንፍና እንደ ኾነ ዛሬም ዕወቁት።

አስተባብሮ እንኳ ቢያውቅ ግእዝ ካማርኛ

ያከለክለዋል ባዕድነቱ ዳኛ።

የባዕድንም ሥራ እንድትረዱት
ሳሌም ተሻግራችኹ ዴር ሥልጣን እዩት፤
ዴር ሥልጣንም ማለት ገደመ ንጉሥ
የኢትዮጵያ ቦታና መቅደስ፤
ይገባኛል ብሎ እንደ ልቅናው
በቱርኮች ትከሻ ግብጥ የወሰደው።
ዋሽቴም እንደኾን በግብጥ በቱርክ
ይታዘቡኝ አርመን ሶርያ ግሪክ።
ያትጋፊኙን ሊቅ አበው ሊቃውንት
በንጉሡ አስጠግተው ሐዬጌ ያሉት
የልቅናውን ስም ጵጵስናውን
ስለ ተቀሙ ነው እንደ ዴር ሥልጣን።
የኒቅያንም ሕግ ጠይቁ ከሰው፤
ፍትሐ ነገሥቱማ ሕገ ወጥ ነው።
ባራተኛው አንቀጽ የሚተቸው ትች
ስንኳን ዐዋቂና ያሥቃል ልጆች።

(፲፩)

(ተ) በጠቀስሽው ኹሉ ምሳሌ ንባብ
ገና አኹን ተረዳን የምክርሽ ጥበብ።
ምክርሽ ኔግሪታ ሮም የሚያሞቅ መጠጥ
ምነው ላፍሪቃ ሰው ለኹሉ ቢሰጥ።

**(ፊ) እናንተ እንጂ ናችኹ ያፍሪቃ ራስ ቅል**
**ባለዘውድ ቋንቋ ባለነጻ አክሊል።**
**ግእዝ ዐማርኛም ኹለቱ ቋንቋች**
**ታላቅ ታናሽ አባይ ያፍሪቃ ወንዞች፤**
**ካፍሪቃ ዐልፈው ተርፈው በባሕር በየብስ**
**ገና ይሰፋሉ እንደግዜር መንፈስ።**
**ስላማርኛና ስለ ግእዝ ክብር**
**ዋዜማ ተቊሟል በብዙ አህጉር።**
**በቀያፋ ልማድ መስሏችኹ ዝንጋዔ**
**ዐደራ እንዳትከዱት ያፍሪቃን ትንሣኤ።**
**ፍጥረቱን ካመድ ላይ ሲያነሣ ሲጥል**
**እግዜርም እንደ ሰው አትርሱኝ ይላል**
**እናንተም ስለግዜር ጸሎት ስታደርሱ**
**ቦ ጊዜ ለኵሉ ያለውን አትርሱ።**

**(፲፪)**

**(ተ) ለልጆች የሚሰብክ የሚያስተምር ሰው**
**በደንጊያ በጡብ እንደሚጥፍ ነው**
**የልጅም ልቡና ጽላተ ኪዳን**
**ከያዘ የማይለቅ የጣፉበትን።**
**(ፊ) አኹንም ይህ ስብከት እንዳይገደፍ**
**በልባችኹ ጽላት ይቀረጽ ይጣፍ።**

**(፲፫)**

**(መምር ፊና ተን ሲዘልፍ)**

**ያገር ፍቅር የሚሉት ጌሾና ብቅል**
**ሆድ ያባውን ኹሉ ያስለፈልፋል።**
**(ፊና ተ) እኛ እናዝንም ከቶ ለፍላፎች ቢሉን**
**የልባችን ዘካ ስንኳን ወጣልን፤**
**ይህነንም ዘካ በየወረዳው**
**ተማሪና መምር ተካፍሎ ይብላው።**
**(መ) ክርክሩን ተዉት ይብቃ ውዝግቡ፤**
**ከፊደላዋሪያ ዝም ብላችኹ ግቡ።**



(፲፯)

# ፊደለ ሐዋርያ።

**ወንጌል ዘማርቆስ፤ ምዕራፍ ዐሥርቱ ኍልቈ እምዐሥርቱ ወሠለስቱ እስከ ዐሥርቱ ወስድስቱ።**

**ወአምጽኡ ኀቤሁ ሕፃናት ከመ ይግስሶሙ ወገሠጽዎሙ አርዳኢሁ ለእለ አምጽእዎሙ። ወርእዮ እግዚእ ኢየሱስ ተምዐ ወይቤሎሙ ኅድጉ ሕፃናተ ይምጽኡ ኀቤየ ወኢትክልእዎ፤ እስመ ለዘከመ እሉ ይእቲ መንግሥተ እግዚአብሔር። አሜን አብለክሙ ዘኢተቀበላ ለመንግሥተ እግዚአብሔር ከመ ሕፃን ኢይበውኣ። ወአንበሮሙ ውስተ ሕፅኑ ወወደየ እዴሁ ዲቤሆሙ ወባረኮሙ።**

## ፊደላዋሪያ።

## የማርቆስ ወንጌል ፲ኛ ምዕራፍ ቁጥር ካ፲፫ እስከ ፲፮።

**ሕፃናትም ወደ ርሱ አመጡ ሊዳስሳቸው፤ ደቀ መዛሙርቱ ግን ያመጧቸውን ተቈጧቸው። የሱስም ባያቸው ጊዜ ዐዘነ አላቸውም፤ ተዉ ሕፃናት ወደኔ ይምጡ አትከልክሏቸው፤ የግዜር መንግሥት እንደነዚህ ላሉ ናትና። እውነት እላችኋለኹ፤ የግዜርን መንግሥት ያልተቀበለ እንደ ሕፃን አይገባባትም። በብቱም አኖራቸው እጁንም ጫነባቸው ባረካቸው።**

<><><><><>

(፲፯)

# የነቈጥና የነጥብ የንባብ ስሞች።

| መልካቸው | ስማቸው። |
|---|---|
| . | ይዘት፤ ወይም ማጥበቂያ። |
| ፡ | ነቊጥ፤ ወይም ነጥብ። |
| ፣ ፥ | ንኡስ፤ ሥረዝ፤ ወይም ነጠላ። |
| ፤ | ዐቢይ ሥረዝ ወይም ድርብ። |
| ። | ነጥብ ፤ ወይም ነጠብጣብ። |

አገባባቸውን ከይዘትና ከንኡስ ሥረዝ በቀር የንባቡ ውስጥ እይ።

የንባብ ትምርት እንደ ዜማ ስልት ሦስት ክፍል ነው።

፩ኛ ግእዝ ፪ኛው ወርድ፤ ፫ኛው ዐቢይ ይባላል። በነዚህ ላይ ደግሞ ቊጥርና ድጋም ሲጨመሩ መላው ፭ ይኾናል። ኹሉም በሕፃን አካኼድ ይመሰላል ቊጥር እንደ መንፏቀቅ፤ ግእዝ እንደ መዳኽ ነው እነዚህ ኹለቱ በሣር በሥንጥር ይነገራሉ። ቊጥር ያንዳንዱን ፊደል ራስ ራሱን በሣር እየነኩ ስሙን መጥራት ነው። ግእዝ፤ ከነቊጥ እስከ ነቊጥ በያንዳንዱ ሣጥን ያሉትን ፊደሎች እንደ መሠረዝ ሣሩን በላያቸው እያሳለፉ በቅርብ በቅርቡ ማጋጠም ነው። ወርድ፤ ዘርፍና ባለቤት ሳቢና ተሳቢ በማዛረፍና በማናበብ የሚወድቅና የሚነሣ ቀለም ለይቶ በሐዘንዚን ቃል እየጮኹ እያስረገጡ ማንበብ ነው። ይኸውም እጅን ተይዞ አቱ ሥግራ ታቱ ሥግራ ወይም ዳዴ አንድ ኹለት እየተባሉ በመኼድና በመራመድ በመወናከር ይመሰላል። አቡጊዳ ወርድ

ንባብ፤ ለተማሪ በጣም ይጠቅማሉ አለነዚህ አለኹለቱ በፊደል በንባብ ቶሎ መሠልጠን አይቻልም። ዐቢይ ንባብ ራስን ችሎ እየተቀናጡ ቶሎ ትሎ እንደ መኼድ ኹሉ በነቍጣ በሥረዝ የተለየውን ቃል ከነጥብ እስከ ነጥብ እንደሚገባው እያሰሙ እያስማሙ ማንበብ ነው። ድጋም ወይም ማነብነብ በሩጫ አካኼድ ይመሰላል።

(፲፯)

# የሱርስትና የዕብራይስጥ የዐረብ የግእዝም ፊደል ከነስሙና ከነቍጥሩ።

| (ሱርስት) | (ዕብራይስጥ) | (ዐረብ) | (ግእዝ) | (አኃዝ) |
|---|---|---|---|---|
| አላፍ ܐ | አሌፍ א | አልፍ ا | አ አልፍ | ፩ |
| ቤት ܒ | ቤት ב | ባእ ب | በ (ጰ) ቤት | ፪ |
| ጎልማ ܓ | ጊሜል ג | ጅም (ገ) ج | ገ ገምል | ፫ |
| ዶላት ܕ | ዳሌት ד | ዳል د | ደ ድልት | ፬ |
| ሄ ܗ | ሄእ ሄይ ה | ሃእ هـ | ሀ ሆይ | ፭ |
| ዋው ܘ | ዋው ו | ዋው و | ወ ዋዌ | ፮ |
| ዛይ ܙ | ዛይን ז | ዛይ ز | ዘ ዛይ | ፯ |
| ሔት ܚ | ሔት ח | ሓእ ح | ሐ (ኀ)ሐውት | ፰ |
| ጤት ܛ | ጤት ט | ጣእ ط | ጠ ጠይት | ፱ |
| ዮድ ܝ | ዩድ י | ያእ ي | የ የማን | ፲ |
| ኮፍ ܟ݂ ܟ | ካፍ כ | ካፍ ك | ካ ካፍ | ፳ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሎማድ ܠ | ላሜድ ל | ላም ل | ለ ላዊ | ፴ |
| ሚም ܡ | ሜም מ | ሚም م | መ ማይ | ፵ |
| ኑን ܢ | ኑን נ | ኑን ن | ነ ነሐስ | ፶ |
| ሤ (ሡ) ምካት ܣ | ሣሜኽ (ሰ) ס | ሢን س | ሠ ሠውት | ፷ |
| ዔ ܥ | ዐይን ע | ዐይን ع | ዐ ዐይን | ፸ |
| ፌ ܦ ܦ | ፌእ פ | ፋእ ف | ፈ (ፐ) ፈፍ | ፹ |
| ጻዴ ܨ | ጻዲ צ | ጻድ ص | ጸ (ፀ) ጸደይ | ፺ |
| ቆፍ ܩ | ቆፍ ק | ቃፍ ق | ቀ ቆፍ | ፻ |
| ሪሽ ܪ | ሬሽ ר | ራእ ر | ረ ርእስ | ፪፻ |
| ሺን ܫ | ሺን (ሠ) ש | ሺን ش | ሰ ሳት | ፫፻ |
| ታው ܬ | ታው ת | ታእ ث | ተ ታው | ፬፻ |

# (፲፰)

# ማስረጃና ማስታወቂያ።

በሱርስቱ ከዚህ ያልታተሙ ፬ ዲቃሎች አሉ። ለዕብራይስጡ በመጨረሻ ቃል የሚገቡ ፭ ዲቃሎች እንዳሉት ለዐረቡም በነቍጣ የተዳቀሉ ፮ ዲቃሎች አሉት፤ ፪ቱ በኀርም ኅና በ**ፀጸ ፀ** አንጻር የተፉት ናቸው ፬ቱን መሰል ስለሌላቸው ትተናቸዋል። እሊህም ፳፪ቱ ፊደላት ዲቃሎቻቸውም ሳይቀሩ ባ፭ ጾታ ተከፍለው በጕረሮና በትናጋ ፣ በምላስና በከንፈር ፣ በጥርስ ይነገራሉ።

| | | |
|---|---|---|
| ፩፤ በጕረሮ | የሚነገሩ | ፭፤ - አ ዐ ሀ ሐ ኀ። |
| ፪፤ በትናጋ | የሚነገሩ | ፬፤ - ገ የ ከ ቀ። |
| ፫፤ በምላስ | የሚነገሩ | ፭፤ - ደ ጠ ለ ነ ተ። |
| ፬፤ በከንፈር | የሚነገሩ | ፮፤ - በ ወ መ ፈ ጸ ፐ። |
| ፭፤ በጥርስ | የሚነገሩ | ፮፤ - ዘ ሠ ሰ ጸ ፀ ረ። |

በጕረሮ የሚነገሩ ያ፭ቱ ፊደላት (**አ ሀ ዐ ሐ ኀ**) ልዩነቱ በመልክና በድምጥ በ፪ ወገን ነው እንጂ፤ በመልክ ብቻ አይደለም፤ ምስጢራቸውም እንደ መልካቸው እየቅል ነው። ራብዓቸውም (**ኣ ሃ ዓ ሓ ኃ**) እንደ ሌላው ዅሉ (**በ - ባ ፡ ገ - ጋ ፡ ደ - ዳ**) ከግእዛቸው ልዩ ነው።

አሀና ዐሐ አንዳንድ ወገን ናቸው፤ ባማርኛ ይወራረሳሉ።

***ሀገር*** = **አገር**፤ ***ሐዲስ*** = ***ዐዲስ***፤ ድምጣቸውም ንኡስና ዐቢይ ይባላል። **ኀ** ደግሞ የ**ሐ** ዲቃላ ሲኾን ድምጡ እንደ መልኩ ልዩ ኹኖ ከካፍ ዲቃላ ከኸ ይስማማል። እንዲህ ስላልነ ግን የግእዙ ኀ ድምጥ ባማርኛ ካልኾነ በቀር

በግእዝ አጠራር ከግእዙ ኸ አይስማማም ከራብዑ እንጂ። **(ኈ-ኻ ፡ ኍ-ኹ ፡ ኊ-ኺ (ኋ) ፡ ኌ-ኼ ፡ ኍ-ኽ ፡ ኖ-ኾ)** ራብዑም **ኋ** ከግእዙ **ኈ** እንደ መልኩ በምሥጢር በድምጥ ልዩ ነው፤ በጣም አፍ ያስከፍታል። የነዚህ ያምስቱ ፊደላት ድምጣቸውና ጠባያቸው ካማሮች ይልቅ በትግሮችና በዐረቦች በዕብራውያን ዘንድ ይታወቃል፤ ለወደ ፊቱ ግን ዐማሮችም ጠንቃቃ መምር ካገኙ ይችን ፊደል ይዘው በመማርና በመጠየቅ ጠንቅቆ ማወቅ ይችላሉ።

## ማስታወቂያ።

እነዚህ አራቱ ተባብረው ተጫፍረው የታተሙ ስለ ፫ ነገር ነው። **፩ኛው**፤ <u>የፊደላት ተራ በሴም ቋንቋ ኹሉ አበገደሀ እንደ ኾነ፤ ሀለሐመሠ እንዳይዶለ ገልጦ ለማስረዳት።</u> **፪ኛው**፤ የግእዝ አካኼድ ጥንታዊ ጥርጊያ ከቀኝ ወደ ግራ እንደ ነበረ፤ እንደ ዛሬው ከግራ ወደ ቀኝ እንዳይዶለ በወንድሞቹ አንጻር ለማሳየት። **፫ኛው**፤ የግእዝ ተማሮች ሌላ ባዕድ ፊደል በማየት ለቋንቋ ትምርት እንዲሣሡና እንዲነሣሡ ነው። ከዚህ የቀረውን ሐተታና ታሪክ፤ የፊደልን ጠባይ ዐመልና ዋየል በመዝገበ ፊደል ተመልከት።

**መዝሙር።**

በስሙ አስዠምሮ ላስጨረሰን ጌታ

ቅዳሴ ውዳሴ ማሕሌትና እልልታ።

ልጆች ተሰብሰቡ ሆሳዕና እንበል

እንደ ሰሌን ይዘን ይህችን ፊደል፤

ኋላ የሚመጣው በሰማይ ደመና

ባቡጊዳ ዕዋል ዛሬ መጥቷልና።

NIGUSS DIGITAL LIBRARY



# ስለደራሲው በጥቂቱ

አለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ በሸዋ ክፍለ ሀገር በይፋትና ጥሙጋ አውራጃ በ፲፰፻፷፬ ዓ.ም. ተወለዱ። ለትምህርት ሲደርሱ በአካባቢያቸው የነበረውን የአገራቸውን ትምህርት ተማሩ። በኋላም ወደ ጎንደር ተጉዘው የመጻሕፍትን ትርጓሜ አጠኑ። በጊዜው የነበራቸው የቀለም አቀባበል፣ የሚስጥር መመራመርና መራቀቅ በጉባኤው ላይ «የቀለም ቀንድ» የሚል ቅጽል ተሰጣቸው።ማናቸው ማናቸው

አለቃ ኪዳነወልድ ከግዕዝና አማርኛ ሌላ ዐረብኛ፣ ዕብራይስጥ፣ ላቲን፣ ሌሎችንም ቋንቋዎች አጠናቅቀው ያውቁ ነበር ። አለቃ ኪዳነወልድ በእየሩሳሌም ለ፳፪ ዓመት ተቀምጠዋል ። በዚህም ወቅት ብሉይና ሐዲስ በሦስት ቋንቋ ጠንቅቀው አመሳክረው ተርጉመዋል ። ኪዳነወልድ ክፍሌ በ፲፱፻፳፮ ዓ.ም. የመጀመሪያውን መዝገበ ፊደል አውጥተው ከልዩልዩ ቋንቋዎች ጋር በማመሳከር አሳትመዋል ። የኢትዮጵያ ፊደል አመጣጡንና ባህሉን በውል አስተባብረው በማቅረባቸውም በጊዜው ተቋቁመው ለነበሩት ትምህርት ቤቶች መመሪያና መማሪያ ለመሆን በቅተዋል ። ቀጥለውም ትንሽ አማርኛ ፊደል ከአረብና ከዕብራይስጥ አቀራኝተው አሳትመዋል ።[1]

አለቃ ኪዳነወልድ በተለያየ ዘይቤ ያቀርቧቸው የነበሩት ግጥሞች ለትውልድ ታላቅ ጥቅም ይሰጣሉ ተብለው የሚገመቱ ናቸው ። እንዲያውም ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪቃ የብዙ ሺሕ ዘመናት ነጻ አገር ባለፊደልና ባለቋንቋ የሆነች እሷ ብቻ ስለሆነች ትውልድ ያገሩን ትምህርት በመጀመሪያ እንዲማር ያካሂዱት የነበረው ቅስቀሳ በቀላሉ የሚታይ አይደለም ። በዓለም ስማቸው የገነነ የሥነ ጥበብ፣ የኪነ ጥበብ ፣ የጽሑፍ ባለአጉዛዎች

የሚደነቁባቸው በራሳቸው ቋንቋ ጽፈው ለዓለም የአቀረቧቸው ሥራዎች ናቸው ይላሉ ።

አለቃ ኪዳነወልድ ለኢትዮጵያ ባላቸው ዐቅም በብሔራዊ ስሜት ተነሳስተው ለታሪክ የሚቀርቡ በርከት ያሉ መጻሕፍት ጽፈው አሳትመዋል ። በተለይም ከዘጠኝ መቶ ገጾች በላይ የሆነው «የሰዋሰው መጽሐፍ» ታላቅ እንደሆነ ይነገራል ። አለቃ ኪዳነወልድ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ታላቅ አስተዋፅኦ ያደረጉ ሰው ነበሩ ።[1]

አለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ በተወለዱ በ ፸፪ ዓመታቸው ፤ ሰኔ ፳፬ ቀን ፲፱፻፴፮ ዓመተ ምሕረት ዐርፈው ደብረ ሊባኖስ ተቀበሩ።[2]

## የደራሲው ሥራዎች

1. ሃይማኖተ አበው ቀደምት (**መልክ ፥ ገድልና ፡ ነገረ ፡ መለኮት**)
2. መዝገበ ፊደል (**መዛግብተ-ቃላት**)
3. አበገደ (**መዛግብተ-ቃላት**)
4. መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ።
5. ፊደልና፡ፊደላዋሪያ፥የልጆች፡አፍ፡መፍቻ።
6. መጽሐፈ ሕዝቅኤል (**የአንድምታ ትርጓሜ**)